# የደም እንጀራ

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ጡት የጣለበት አንዱ ምግብ ቢኖር እንጀራ ነው።መልክና የሚጋገርበት ምጣድና የእህል አይነት የተለዩ ቢመስልም ሁሉም እንደአቅሙ በማባያ ወጥ እያጠቀሰ፣በፍትፍት፣በድርቆሽ ፍርፍር መልክ ወይም በርበሬና ጨው ነስንሶበት ይመገበዋል።በአገራችን በኢትዮጵያ ከነጭ፣ሰርገኛና ጥቁር ጤፍ፣ከገብስ፣ከማሽላ፣,ከበቆሎ፣ከዳጉሳ፣በነጠላና ቅልቅል ተጋግሮ መብላት ከረጅም ጊዜ በፊት የተለመደ የአመጋገብ ባህል ሆኖ የቆዩ ነው።

እንደአቅሙ በቀን ከአንድ ጊዜ እስከ ሦስት ጊዜ ለሚቀርበው ማዕድ፣ እንጀራ አንጋፋና በሁሉም ዘንድ የማይሰለች ተመራጭ ምግብ ነው።በቤት በሞሰብ በጉዞ በአገልግል አብሮ  ቀርቦ መብላትና መጎራረስም የዚሁ አመጋገብ ዋናው መልክና ጣዕሙ ነው።እንጀራ ሆድ ከሞምላቱና እርሃብ ከማሶገዱም በላይ ክብር ያለው፣ለሌላ የማይነፍጉት፣የፍቅርና ቃል ኪዳን ማሰሪያ ነው፤አብሮ ማድ የቀረበና አብሮ የበላ አይካካድም፣ያጎረሰኝ እጁ/እጇ ይታዘበኛል፣ይጥለኛል!  የሚል ፈሪሃ እግዚአብሔርና ስነምግባር ያሰፍናል።

የሰው ልጅ ምግብ በልቶ ማደር የተፈጥሮ መብቱና ስጦታ ነው።ካለምግብ ሊኖር አይችልም።የየአገሩ ሕዝብ በከባቢው ከሚመረቱና ከሚበቅሉ አዝርእቶች በልማድ በወረሰውና ባሳደገው አሰራርና ዝግጅት መጠንና መልክ አዘጋጅቶ ይበላል።ኢትዮጵያውያንም በአገራቸው መሬት የበቀለውን እህል በተለያየ መልክ ተዘጋጅቶ የመብላት ባሕል አላቸው።ዋናውና በሰፊው የተለመደው እንጀራና በእንጀራ መልክ እየጋገሩ የሚያዘጋጁት ምግብ ነው። እንጀራን ለመብላት ማምረት ወይም መሸመት ያስፈልጋል፤የገጠሩ ነዋሪ በማምረት ሲያገኘው ከተሜውና ከእርሻ ሙያ ጋር ያልተያያዘው ደግሞ እህሉን ገዝቶ አዘጋጅቶ ይመገበዋል።

የዛሬውን አያድርገውና!በአገራችን ባሕል እንጀራ የሚሸጥ ሸቀጥ አልነበረም፣ እንጀራ ተካፍለው፣ያለው ለሌለው አካፍሎ የሚበሉት፣የደግነትና ያክብሮት መግለጫ ባህል ነበር።እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ገዝቶ ወይም ሆቴል ቤት ገብቶ መብላትም አስነዋሪ ነበር። በኢትዮጵያ ውስጥ ሆቴል ቤት ከአገሩና ከቤቱ ለወጣ ማረፊያና መመገቢያ እንጂ ለተወላጁ ታስቦ የተሠራ አልነበረም። የመጀመሪያው የጥንቱ የእቴጌ ጣይቱ ሆቴል የውጭ አገር ሰዎች ወደአገራችን በብዛት መምጣት በጀመሩበት ጊዜ ለማስተናገድና ለማረፍ ታስቦ የተሠራ ነበር።በተለይ ከጣሊያን ወረራ በኋላ የሆቴል ቤት እንደ አንድ የንግድ ተቋም ለመታየት በቃ።ከሃምሳ ዓመት ወዲህም ሆቴል ቤት እየተስፋፋ ፣እንጀራም በገባዬ ላይ ሸቀጥ ሆኖ መውጣት ጀመረ።ተዲያ ገዝቶ የሚበላው ከተሜና ትዳር አልባ የሆነው ወንደላጤ እንጂ ባለጎጆ(ባለትዳር)  አልነበረም።አሁን ግን ከኢትዮጵያ አልፎ ድንበር ተሻግሮ በሱቅ መደርደሪያ ላይ  ለሽያጭ ከሚቀርቡት የአገር ምርቶች አንዱ ሆኗል።

የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር፣የእርሻ መሬት ከገበሬው ሲነጠቅ፣ለም መሬት ለሌላ የውጭ አገር ባለጸጎች እየተሸጠና እየተሰጠ ለውጭ ገበያና ለፋብሪካ ምርት ጥሬ ዕቃ ማምረቻ ጥጥ፣ጫት፣አበባ፣የቢራ እህል፣ የነዳጅ በቆሎ…ወዘተ ቅድሚያ ሲሰጠው፣ድርቅና የአየር ለውጥ ሲከሰት፣ ለምግብ የሚሆን እህል ለማምረት አዳጋችና አስቸጋሪ በመሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በርሃብ አለንጋ በመገረፍና በመርገፍ ለተደጋጋሚ እልቂት ተዳርገዋል።እርሃብ የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ገጿ ሆኗል።የምርት እጥረትም በመከሰቱ ለምግብ እህል የሚከፈለው ገንዘብ ከብዙሃኑ አቅም ጋር የተመጣጠነ አይደለም።ብዙ ሚሊየን ሕዝብ በውጭ አገር እርዳታና ዳረጎት ባይጠግብም በቀን አንድ ጊዜ ቀምሶ ኗሪ ሆኗል።

የአንድ አገር መንግሥት ተግባርና ሃላፊነት ሌላው ቢቀር  በቅድሚያ  የሕዝቡን የምግብ አቅርቦት እንዲሟላ፣ጤናው እንዲጠበቅና የመጠለያ ቤት እንዲኖረው ማድረግ ነው።ይህን ማሟላት የማይችል መንግሥት እንደመንግሥት መቆጠርና በሥልጣን ላይ መቀመጥ አይገባውም።በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት ግን የሕዝቡን ጥያቄ የሚያሟላ ሳይሆን ከሕዝብ ጉረሮ እየነጠቁ እንጀራና ሌላም አይነት የተዘጋጀ ምግብ(የተነጠረ ቅቤ፣በርበሬ፣ቋንጣ፣በሶ…ወዘተ)  በውጭ አገር የሚሸጡ ጨካኝና አረመኔዎች የተሞሉበት፣የተሰገሰጉበት ጉረኖ(ዋሻ) ነው።እነዚህ ለሕዝብ ደንታ የሌላቸው ነፍሰበሎች የሰውን ስነልቦናና አገራዊ ስሜት እየተጠቀሙ ስለጥራቱ ቁጥጥር የማይደረግበትን ምግብ እያዘጋጁ በውጭ አገር ገበያ በከፍተኛ ዋጋ ይሸጣሉ።በቅቤው ላይ የተነጠረ ላት፣በማሩ ላይ ሙዝ፣በበርበሬው ላይ ቀይ ሸክላ፣እየቀላቀሉ መሸጣቸው የታወቀ ሲሆን በጥቁር ጤፍ ዱቄትና እንጀራም ላይ ጥቁር አፈር ወይም ዋልካ እንደሚቀላቅሉበት ይሰማል።

በዚህ ዓይን ያወጣ የእንጀራ ንግድ  የተሳተፉት ጋጋሪዎች በድህነት ቀንበር የታሹ፣በችግር የሚኖሩ ድሆች ሲሆኑ የሚያገኙት ክፍያም በወር ከሰባት መቶ እስከ አንድ ሺህ ብር ቢደርስ ነው።በቀን አንድ ኩንታል(100 ኪሎ)ማለትም ከአምስት  መቶ በላይ እንጀራ የመጠፍጠፍ ግዴታ አለባቸው፣ከሚጋግሩት እንጀራ ለራሳቸው ወይም ለቤተሰባቸው አንዷት እንጀራ እንዲወስዱ አይፈቀድላቸውም።ያ በጋለ ምጣድ ተለብልበው ፣ጉልበታቸው እስኪብረከረክና  ወገባቸው እስኪዝል ድረስ የሚጋግሩት እንጀራ ዓይናቸው እያየ በላስቲክ ተጠቅሎ በአውሮፕላን ተጭኖ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ሲዘጋጅ ምራቃቸውን እየዋጡ ዓይናቸው እንባ ቋጥሮ ከመታዘብ ሌላ ምንም አይተርፋቸውም።ያ፣ከንጋት እስከምሽት የጋገሩትን እንጀራ በውጭ አገር ገዝቶ የሚመገበው በየአጋጣሚው አገሩን ለቆ የወጣው ወገናቸው ነው፡፤በተለይም ስለሰው ልጅ መብት እከራከራለሁ፣ስለኢትዮጵያውያን መብትና እኩልነት እታገላለሁ፣ለዲሞክራሲና ለነጻነት ስል ተሰደድኩ፣ዘረፋና፣ብዝበዛን የምቃወም የፖለቲካ ስደተኛ ነኝ ብሎ በያገሩ መኖሪያ ፈቃድ ያገኘው ዜጋ አዙሮ ማየት ተስኖት የጥቅሙ ተካፋይ ሆኗል።

እርግጥ ነው አንድ ሰው ካገሩ እርቆ ሲኖር የአገሩ ምግብ፣አለባበስና ባህል ይናፍቀዋል፣ያምረዋል።ያንን አምሮቱን ለመወጣት የሚችልበት ከሌላው ጉዳት ጋር ያልተያያዘ ዕድልና አጋጣሚ ካለ ቢጠቀምበት አያስነውርም።ነውሩ በአገሩ ላይ ወገኑ የማያገኘውንና የተነፈገውን በኮንትሮባንድ ነጋዴዎች አማካኝነት ገዝቶ መጠቀሙ ነው። ያገሩ ገበያ ተራቁቶና ወገኑ ለመብላት የተነፈገውን እሱ ገዝቶ ለመብላት ገንዘብ አውጥቶ ሲገዛ የወንጀሉ ተባባሪ መሆኑን ማወቅ ይገባዋል።የጋገሪዎቹን ስቃይና መከራ፣የርሃብተኛ ወገኖቹን የቀን ተቀን የስቃይ ኑሮ ቢያስበው እንኳንስ ከአገሩ የመጣ የደም እንጀራ ቀርቶ ሌላም እህል ለመብላት አሞቱ እሺ አይለውም ነበር።

አንድ ሰው ወደሌላ አገር ሲሰደድና ወጥቶ ሲኖር፣ከገባበት አገር ባህል፣ቋንቋ፣ምግብና አስተሳሰብ ጋር ውህደት ማድረግ ይገባዋል።በሌላ አገር ሕዝብ መካከል እየኖሩ የራስን ቋንቋ፣ ባህል፣አመጋገብና አስተሳሰብ ብቻ ተሸክሜ ልኑር ቢሉ በራስ ላይ ችግር መፍጠር ፣ከማህበረሰቡ መገለልና መነጠል፣ለዘረኞችም የጥቃት ኢላማ ይሆናል።የራስን ሙሉ ለሙሉም ሳይጥሉ ካሉበት አካባቢ ጋር ተመሳስሎ ማደሩ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም።የአገር ምግብ ወይም እንጀራ አምሮቱ ቢጠና በከባቢው ባሉ የእህል ዱቄቶች በቤት ውስጥ መጋገር ይቻላል፣ቀደም ሲል የመጣነውም በዚያ መልክ ነበር የእንጀራ አምሮትና ናፍቆታችንን የምንወጣው።አሁን ደግሞ በአሜሪካ አገር ጤፍ ማምረት ተጀምሯል።ይህ ሁሉ ዕድል ባለበት ሁኔታ ከደሃይቱ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጉሮሮ እየተነጠቀ፣በድሆች ላብና ጉልበት ተጋግሮ ለሚመጣ እንጀራና የምግብ አይነት ከሚገባው በላይ ከፍሎ መጠቀም ኢሰብአዊ አድራጎት ከመሆኑም በላይ በብልጣብልጥ ነጋዴዎች የሚዘረፍ ጅል መሆን ነው።የጤና ግዴታ ሆኖበትም የጤፍ እንጀራ ለመብላት የሚገደደውም በሽተኛ ከዚህ አላመለጠም።መታወቅ ያለበት ግን ለጤና የሚጠቅመው ምግብ ጥቁር ጤፍ ብቻ አለመሆኑ ነው።ጥቁር ጤፍ የማይበሉ ጤነኛ ሕዝቦች እንዳሉ ማሰብና ማየት ይረዳል።ከጤፍ የሚገኘው ንጥረነገር ወይም ፕሮቲን ከሌሎች የእህል ዘሮች፣አታክልትና ፍራፍሬዎች ይገኛል።አመጋገብን በመለወጥ ጤናን መጠበቅና ማስተካከል ይቻላል።

አሁን በአገር ቤቱ የባልትና ሱቅ የሚሸጠው የእንጀራ ዋጋ ነጭ አራት ብር፣ሰርገኛ ሶስት ከሃምሳ፣ጥቁር ሶስት ብር ሲሆን ብዙ ፈላጊ ስለሌለው የሚጋገረው በትእዛዝ ነው።ከኢትዮጵያ ውጭ በየአገሩ የሚታየው የእንጀራ ሽያጭ በጣም ይዘገንናል።ከሚጠየቅበት ዋጋ በተጨማሪ እንጀራነቱ የሚያጠራጥር፣ እንደ ስስ ወረቀት የመነመነ፣እፍ ቢሉት ብን የሚል፣ ወድቆ የማይነሳ፣አይንና ቂጡ የማይለይ፣ሲያዩት አሞት(አፒታይት)የሚዘጋ ፣በስስት የተጋገረ፣ የችግራችንንና የድህነታችንን መጠን የሚያሳይ ከመሆኑ በተጨማሪ በአውሮፓ(አመስተርዳም) ለአምስት እንጀራ እስከ አስራሁለት ኤሮ(ከ 300-350 የኢትዮጵያ ብር)በአሜሪካ በዋሽንግተን ዲሲ ለአራቱ እንጀራ 7 ዶላር( 154 የኢት.ብር) በስዊድን፣ስቶክሆልም አምስት እንጀራ 100 ክራውን(250 የኢትዮጵያ ብር) እንግሊዝ አገር በለንደን ሶስት እንጀራ 5 ፓውንድ (በኢትዮጵያ 130 ብር) በካናዳ ፣ቶሮንቶ ሶስቱ እንጀራ በ 6.50 የካናዳ ዶላር(113.75 የኢትዮ.ብር)ይቸበቸባል።የተጋገረው ብቻ ሳይሆን ዱቄቱም እየወጣ በከፍተኛ ዋጋ ይሸጣል።ለምሳሌም በሆላንድ በኪሎ አምስት ኤሮ(130 የኢትዮ.ብር)በመቶ ኪሎ አምስት መቶ ኤሮ(13,000

የኢትዮ.ብር) ይቸበቸባል።በዚህ መልክ በየአገሩ የሰበሰቡትን በአገር ቤት የጥቁር ገበያ ሲለውጡትና በ 2800 የኢትዮጵያ ብር የተገዛው መቶ ኪሎ ጤፍ፣ማስፈጫው፣የጋጋሪው፣ የማስጫኛውና የውጣ ውረዱ ተቀንሶ ምን ያህል ትርፍ እንደሚገኝበት ለገማች እተወዋለሁ።በንግዱ በሞኖፖል የተሰማሩት ባለሥልጣኖቹና ቤተሰቦቻቸው ናቸው፤ለሚጭኑት መጠነብዙ ጭነት ለአየር መንገዱ የሚከፍሉት አይኖርም ቢኖርም የተወሰነ ነው፤አየር መንገዱን የግል አጋሰሳቸው አድርገውታል ማለት ይቻላል።

አገር ውስጥ ሕዝብ ጠግቦ፣ገበያው ተትረፍርፎ ቀሪው ለሽያጭ ቢወጣ ተቃውሞ ማድረግ ተገቢ አይሆንም።ግን በአሁኑ ሁኔታ ከአገር እየወጣ በውድ ዋጋ የሚሸጠውንና ገንዘቡ ለአገር እድገት ሳይውል በውጭ ባንክ የሚጠራቀመውን የዘረፋ ተግባር መቃወምና ለዘረፋው ተባባሪ አለመሆን የኢትዮጵያዊነት መለኪያ ነው።በድሆች ስቃይና ድካም የተዘጋጀ፣ከተራበው ሕዝብ ጉረሮ እየተነጠቀ በተያዘው መንገድ እንጀራ ገዝቶ መብላትም የደም እንጀራ እንደመብላት ይቆጠራል።በየአገሩ የንግድ ሥራ ተሰማርታችሁ ከኢትዮጵያ የሚመጣውን የምግብ ሸቀጥ ተረክባችሁ የምትሸጡትም በእጅ አዙር ለማን እንደምታገለግሉ እወቁት።ምንም እንኳን ነግዶ ማደር የኑሮ ግዴታ ቢሆንባችሁም የማንን ለማን እንደምትሸጡ ከግምት ውስጥ አስገቡት።በተጨማሪም የምግቡ ጥራት ጉድለት በተጠቃሚው ላይ አደጋ ሊያደርስ ስለሚችልና እናንተንም ተጠያቂ ስለሚያደርጋችሁ ለጥራቱ ዋስትና ማረጋገጫ ይኑራችሁ።እርግጥ ነው በኢትዮጵያ በቀላሉ በሙስና ማህተም የሰፈረበት ማረጋገጫ ማውጣት በጣም ቀላል ስለሆነ ልትታለሉ ትችላላችሁ።በምትኖሩበት አገር የምትሸጡት ሸቀጥ በተለይም ምግብ ለደህንነቱና ጥራቱን የጠበቀ ለመሆኑ ማስመርመርና ሕጋዊ የጤና ጥበቃ መስሪያ ቤት ማረጋገጫ መጠየቅ ይኖርባችኋል።ተጠቃሚውም ለሚገዛው የምግብ ሸቀጥ ለደህንነቱ በሚኖርበት አገር መስሪያ ቤት የተሰጠውን የደህንነት ማረጋገጫ ማየትና ማረጋገጥ ይኖርበታል።ተገኘ ብሎ ማግበስበሱ በራስ ላይ መፍረድ ነው።

የስርዓቱን ሁለገብ ዘረፋና ብዝበዛ ከመተባበር ይልቅ ተባብረን እናክሽፍ!

አገሬ አዲስ

http://www.ethiopanorama.com